የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARITGAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፶፬
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፮

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 54
ADDIS ABABA- 19th July, 2004

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፱/፲፱፻፺፮ ዓ.ም
የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ...ገጽ ፪ሺ፮፻፷

## CONTENTS

Proclamation No. 409/2004
Refugee Proclamation.... Page 2660

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፱/፲፱፻፺፮

## የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ

ኢትዮጵያ ለስደተኞች መጠጊያና ከለላን የምትሰጥ፣ ሁኔታዎች በፈቀዱ ጊዜ ሁሉ ደህንነታቸውንና ክብራቸውን ተጠብቆ በራሳቸው ፈቃድ ወደሀገራቸው እንዲመለሱ የምታበረታታ በመሆኑ፣

ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ ጁላይ ፳፰ ቀን ፲፱፻፶፩ በጄኔቫ የፀደቀው የስደተኞች ኮንቬንሽን፣ እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ ፴፩ ቀን ፲፱፻፷፯ የፀደቀው የስደተኞች ፕሮቶኮልና እ.ኤ.አ. ሴፕቴምበር ፲ ቀን ፲፱፻፷፱ በአዲስ አበባ የፀደቀውና የአፍሪካ ስደተኞችን ችግር የተወሰኑ ገፅታዎች የሚገዛው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ኮንቬንሽን አባል በመሆኗ፤

ከላይ የተገለፁ ዓለም አቀፍ የሕግ ሰነዶችን በሚገባ ስራ ላይ ለማዋል ብሔራዊ ሕግ በማውጣት ሕጋዊና አስተዳደራዊ መዋቅር በመመስረት ስደተኞችን መቀበል፣ ደህንነታቸውን መንከባከብና በተቻለ መጠን የዘለቄታ መፍትሔ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

## PROCLAMATION NO. 409/2004

## REFUGEE PROCLAMATION

**WHEREAS**, Ethiopia is providing asylum and protection to refugees and promoting their voluntary repatriation in safety and dignity whenever conditions permit,

**WHEREAS**, Ethiopia is a party to the Convention Relating to the Status of Refugees done at Geneva on 28 July 1951, the Protocol Relating to the Status of Refugees of 31 January 1967 and the OAU Convention Governing the Specific Aspects of Refugee Problem in Africa, done at Addis Ababa on 10 September 1969.

**WHEREAS,** it is desirous to enact national legislation for the effective implementation of the aforesaid international legal instruments, establish a legislative and management framework for the reception of refugees, ensure their protection, and promote durable solutions whenever condition permit;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 4·80

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit G. P.O Box 800

## ክፍል አንድ
## ጠ ቅ ላ ላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፬፻፱/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ ወይም የሐረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣ በዚህ አዋጅ፣

፩/ "ባለሥልጣን" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፮ ፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፮/፩/ መሠረት የተቋቋመው የደህንነት፣ የኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን ነው፤

፪/ "የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር" ማለት በኢትዮጵያ የሚገኘው የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽሕፈት ቤት ነው፤

፫/ "የስደተኞች ኮንቬንሽን" ማለት እ.ኤ.አ ጁላይ ፳፰ ቀን ፲፱፻፶፩ በጄኔቫ የፀደቀው የስደተኞች ኮንቬንሽን እና እንደ እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ ፴፩ ቀን ፲፱፻፷፯ የፀደቀው ፕሮቶኮል ማለት ነው፤

፬/ "የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የስደተኞች ኮንቬንሽን እና እንደ እ.ኤ.አ ጃንዋሪ ፴፩ ቀን ፲፱፻፷፯ የፀደቀው ፕሮቶኮል" ማለት እ.ኤ.አ ሴፕቴምበር ፲ ቀን ፲፱፻፷፱ በአዲስ አበባ የፀደቀውና የአፍሪካ ስደተኞችን ችግር የተወሰኑ ገፅታዎች የሚገዛው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ኮንቬንሽን ማለት ነው፤

፭/ "የዜግነት አገር" ማለት ስደተኛው ዜጋ የሆነበት አገር ማለት ነው፤

፮/ "የቀድሞ መደበኛ መኖሪያ አገር" ማለት አንድ ሰው በቋሚነት ይኖርበትና ጥበቃውንም ያገኘበት የነበረ አገር ማለት ነው፤

፯/ "ስደተኛ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ ወይም አንቀጽ ፲፱ የተጠቀሰውን መስፈርት የሚያሟላ ሰው ነው፤

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Refugee Proclamation No. 409/2004."

### 2. Definition

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:-

1) "Authority" means the Security, Immigration and Refugee Affairs Authority established by Proclamation No. 6/1995 Article 6(1)

2) "United Nations High Commissioner for Refugees" means the Office in Ethiopia of the United Nations High Commissioner for Refugees.

3) "The Refugee Convention" means the Convention Relating to the Status of Refugees done at Geneva on 28 July 1951 and the protocol ratified on 31st January, 1967

4) "The OAU Refugee Convention" means the OAU Convention Governing the Specific Aspects of Refugee Problems in Africa, done at Addis Ababa on 10 September 1969

5) "Country of Nationality" means a country, which the refugee is a national.

6) "Country of former habitual residence" means the country where a person established himself permanently and which enjoyed its protection.

7) "Refugee" means any person or group of persons who full fills the criteria under the Provisions of Article 4 or Article 19 of this Proclamation

፰/ "የቤተሰብ አባል" ማለት፣

/ሀ/ የስደተኛው ባል ወይም ሚስት፣
/ለ/ ከአስራ ስምንት ዓመት በታች የሆነ ያላገባ የስደተኛው ልጅ ማለት ነው፣

፱/ "እውቅና ያገኘ ስደተኛ" ማለት፣

/ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ መሠረት በስደተኛነት እውቅና ያገኘ ወይም፣
/ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ ድንጋጌዎች መሠረት ስደተኛ ናቸው የተባሉ ሰዎች ቡድን አባል የሆነ ነው፣

፲/ "ጥገኝነት ጠያቂ" ማለት በድንበር ወይም በጠረፍ ላይ ሆኖ ጥገኝነት ጠያቂ መሆኑን ያስታወቀ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ የስደተኝነት እውቅና እንዲሰጠው ሥልጣን ላለው አካል አመልክቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሚጠብቅ ማንኛውም ሰው ነው።

## ክፍል ሁለት
## ጠቅላላ መርሆዎች

### ፫. ልዩነት ስለአለመደረጉ

ይህ አዋጅ በዘር፣ በኃይማኖት፣ በዜግነት፣ በአንድ የሕብረተሰብ ክፍል አባልነት ወይም በፖለቲካ አስተሳሰብ ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ተፈፃሚ ይሆናል።

### ፬. የስደተኛነት መስፈርት

ማንኛውም ሰው፣

፩/ በዘሩ፣ በኃይማኖቱ፣ በዜግነቱ፣ በአንድ የሀብረተሰብ ቡድን አባል በመሆኑ ወይም በፖለቲካ እምነቱ ምክንያት በእርግጥ /በተጨባጭ/ ማሳደድ ወይም አደጋ ወይም እንግልት ወይም ስቃይ ይደርስብኛል ብሎ በመስጋቱ ምክንያት ከዜግነት አገሩ የተሰደደና በነዚሁ ክስተቶች ምክንያት የዜግነት አገሩን ጥበቃ ለማግኘት ያልቻለ ወይም ያልፈለገ እንደሆነ፤
፪/ ዜግነት የሌለው ከሆነ በዘሩ፣ በኃይማኖቱ፣ በአንድ የተወሰነ ቡድን አባል በመሆኑ ወይም በፖለቲካ እምነቱ ምክንያት በእርግጥ /በተጨባጭ/ ማሳደድ ወይም አደጋ ወይም እንግልትና ስቃይ ይደርስብኛል ብሎ በመስጋት ከቀድሞ መደበኛ የመኖሪያ ሥፍራው ለቆ የተሰደደና እና ወደቀድሞ መደበኛ የመኖሪያ ሥፍራው መመለስ ያልቻለ ወይም ያልፈለገ እንደሆነ፤ ወይም

8) "The Family Members" means:-

a) any spouse of the refugee, and
b) any unmarried child of the refugee under the age of eighteen years.

9) "Recognized Refugee" means a person who:-
a) has been recognized as a refugee in terms of Article 4 of this Proclamation or
b) is a member of group of persons declared to be refugees in terms of Article 19 of this Proclamation.

10) "Asylum-seeker" means any person who presents himself at the border or frontier claiming to be a refugee or any person is in Ethiopia and who has lodged an application with the competent authorities for recognition as a refugee and is awaiting a final decision on his application.

## Part Two
## General Principles

### 3. Non-discrimination

This Proclamation shall be applied without discrimination as to race, religion, nationality, membership of a particular social group, or political opinion.

### 4. Refugee Criteria

Any person shall be considered as refugee where:

1) owing to a well-founded fear of being persecuted for reasons of race, religion, nationality, membership of a particular social group or political opinion he is outside his country of nationality and is unable or, owing to such fear, is unwilling, to avail himself of the protection of that country;

2) not having a nationality and being outside of his former habitual residence, he is unable, or owing to a well-founded fear of being persecuted for reasons of race, religion, membership of a particular social group or political opinion, he is unwilling to return to it; or

፫/ ከአፍሪካ አገሮች የሚመጣ ስደተኛ በሆነ ጊዜ በውጭ ወረራ፣ በግዛት መያዝ፣ የትውልድ ወይም የዜግነት አገሩን ሕዝባዊ ሥርዓት በከፊልም ሆነ በሙሉ በሚያናጋ ከባድ ክስተት ምክንያት ከትውልድ ወይም ከዜግነት አገሩ ውጭ ጥገኝነት ለመጠየቅ ሲል መደበኛ መኖሪያ ሥፍራውን ለመልቀቅ የተገደደ እንደሆነ፤

እንደ ስደተኛ ይቆጠራል።

## ፭. እንደስደተኛ ስላለመቆጠር

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ሰው፣

፩/ ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ሰነድ ውስጥ እንደተደነገገው በሰላምና በሰብዕና ላይ ወንጀል ወይም የጦርነት ወንጀል ስለመፈጸሙ፤

፪/ ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት የፖለቲካ ወንጀል ሳይሆን ሌላ ከባድ ወንጀል ስለመፈፀሙ፤

፫/ የተባበሩት መንግሥታት ወይም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት፣ የአሁኑ የአፍሪካ ህብረት ቻርተሮች፣ ውሳኔዎች ወይም አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሰነዶቻቸው ውስጥ የተካተቱ ዓላማዎችንና መርሆዎችን በመጣስ ጥፋተኛ ስለ መሆኑ አሳማኝ ምክንያቶች የተገኙ እንደሆነ፣ ወይም

፬/ ከአንድ ዜግነት በላይ ኖሮት በነዚህ የዜግነት አገሮች በሚሰጠው ጥበቃ በአንዱ አገር ተጠቃሚ ያልሆነና በዚህም ጥበቃ ላለመጠቀም በቂና ተገቢ ምክንያት የሌለው እንደሆነ፤

እንደስደተኛ አይቆጠርም።

## ፮. በስደተኛነት የተሰጠ እውቅናን ስለማንሳት

፩/ ባለሥልጣኑ በማንኛውም ጊዜ ቢሆን አንድ በስደተኛነት እውቅና ያገኘ ሰው እውቅናውን ማግኘት ያልነበረበት ወይም ስደተኛነቱ ቀሪ መሆኑን ጥብቅ በሆነ ሁኔታ የተገነዘበ እንደሆነ ስለሁኔታው ለስደተኛው በጽሁፍ በማስታወቅና ጉዳዩን አቅርቦ እንዲያስረዳ በመፍቀድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለስደተኛው ተሰጥቶት የነበረውን ዕውቅና ሊሠርዝ ይችላል፤

3) owing to external aggression, occupation, foreign domination or events seriously disturbing public order in either part or the whole of his country of origin or nationality, he is compelled to leave his place of habitual residence in order to seek refuge in another place outside his country of origin or nationality, in case of refugees coming from Africa.

## 5. Exclusion from Refugee Status

Notwithstanding the provision of Article 4 of this Proclamation a person shall not be considered as a refugee for the purposes of this Proclamation if there are serious reasons to believe that:

1) he has committed a crime against peace, a war crime or a crime against humanity as defined in any international instrument to which Ethiopia is a party and which has been drawn up to make provision in respect of such crimes;

2) he has committed a serious, non-political crime outside Ethiopia prior to his entry into Ethiopia;

3) he has been guilty of acts contrary to the purposes and principles of the United Nations or the Organization of African the now African Unity as embodied in the charter, resolutions or other relevant instruments of those bodies; or;

4) having more than one nationality, he has not availed himself of the protection of one of the countries of which he is a national and has no valid reason, for not having availed himself of its protection.

## 6. Withdrawal of Recognition of Refugees

1) If at any time the Authority considers that there are serious ground for believing that a person who has been recognized as a refugee should not have been recognized or has ceased to be a refugee , it may cancel the refugee status given after notifying the refugee concerned in writing and giving him the opportunity to explain about the issue.;

፪/ ስውሳኔው የተሰረዘበት ስደተኛ ውሳኔውን በሰማ በ፴ ቀናት ውስጥ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ መሠረት ለተቋቋመው ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፤

## ፯. እንደስደተኛ መቆጠር ስለሚያበቃበት ሁኔታ

ማንኛውም ሰው፣

፩/ በራሱ ፍላጎት በዜግነት አገሩ በሚሰጥ ጥበቃ መልሶ ተጠቃሚ የሆነ እንደሆነ፤

፪/ የሚደርስበትን መሰደድ በመፍራት ለቆት በወጣው አገር ወይም በቋሚነት በሚኖርበት አገር ውስጥ ራሱን መልሶ ያቋቋመ እንደሆነ፤

፫/ የኢትዮጵያን ወይም የሌላ አገር ዜግነት አግኝቶ በዚሁ በአዲሱ የዜግነት አገሩ በሚሰጥ ጥበቃ ተጠቃሚ የሆነ እንደሆነ፤

፬/ በስደተኛነት እውቅና እንዲያገኝ ምክንያት የነበሩ ሁኔታዎች የቀሩ ወይም የተለወጡ ሆነው፤

ሀ/ በዜግነት አገሩ የሚሰጠውን ጥበቃ ባለመጠቀም አቋሙ የቀጠለ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ዜግነቱን አጥቶ ከሆነ ወደ ቀድሞ መደበኛ መኖሪያ አገሩ አልመለሰም ለማለት የሚያስችል ሁኔታ የሌለ እንደሆነ፣

እንደስደተኛ መቆጠሩ ቀሪ ይሆናል።

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፬ ስር በተገለጹ ምክንያቶች ለደህንነቱ በመፍራት በዜግነት አገሩ ወይም በቀድሞ መደበኛ መኖሪያ አገሩ በሚሰጥ ጥበቃ ለመጠቀም ካለመፈለግ የሚመነጩ አስገዳጅ ምክንያቶችን ማቅረብ በሚችል ስደተኛ ላይ ተፈፃሚ አይሆኑም።

2) Any person aggrieved by the decision of the Authority can appeal within 30 days of receiving the decision to appeal hearing council, established in accordance with Article 15 of this Proclamation.

## 7. Cessation of Refugee Status

Any person shall cease to be considered as refugee if:

1) he has voluntarily re-avails himself of the protection of the country of his nationality;

2) he has voluntarily re-establishes himself in the country which he left or outside of which he remained owing to fear of persecution;

3) he has acquired the nationality of Ethiopia, or that of another country and enjoys the protection of Ethiopia or the country of his new nationality: or

4) Despite the circumstances in connection with which he was recognized as a refugee, have ceased to exist:

   (a) continue to refuse to avail himself of the protection of the country of his nationality: or

   (b) if he has lost his nationality or has no nationality, and is able to return to the country of his country of former habitual residence, but continue to refuse to do so.

5) The provisions of this Article shall not apply, however, to a refugee falling under Article 4 of this Proclamation who is able to invoke compelling reasons arising out of previous persecution or fear for his safety for the reasons set out in Article 4, for refusing to avail himself of the protection of the country of his nationality or country of his former habitual residence.

## ፰. የሁኔታዎች መሠረታዊ ለውጥ

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ የተመለከቱት መሠረታዊ ለውጦች በዚህ አዋጅ መሠረት የስደተኝነት እውቅና ባገኘው ሰው ወይም ሰዎች የዜግነት አገር ወይም የቀድሞ መደበኛ መኖሪያ ቦታቸው መከሰቱ ከታመነ የባለሥልጣኑ ኃላፊ ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር ጋር በመተባበር ለዚሁ ተግባር አፈፃፀም ሲባል የሚዘጋጀውን ልዩ ሥነሥርዓት መሠረት በማድረግ እንዲሁም በመጀመሪያ የስደተኝነት እውቅና ለመስጠት ምክንያት የሆኑ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በተከሰተው ለውጥ ጠባይና በቆይታው ላይ ምርመራና ማጣራት እንዲካሄድ ያደርጋል፤

፪/ ከዚህ ምርመራና ማጣራት በኋላ ባለሥልጣኑ ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር ጋር በመተባበር ለሰውየው ወይም ለሰዎቹ ቡድን የተሰጠው እውቅና መቅረት አለመቅረቱን ይወስናል፤

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት ስደተኝነት ቀሪ እንዲሆን የሚሰጥ ውሳኔ የስደተኝነት ቀሪ መሆን በስደተኛው ወይም በስደተኞቹ ላይ ስለሚያስከትለው ውጤት እንዲሁም እያንዳንዱ ስደተኛ ስላለው ይግባኝ የማቅረብ መብት እንዳለው ማመልከት አለበት።

## ፱ ተገዶ ስላለመመለስ

፩/ ማንኛውም ሰው ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ በመከልከሉ ወይም ከኢትዮጵያ እንዲባረር ወይም ወደመጣበት እንዲመለስ በመደረጉ ወይም በማናቸውም ሌላ እርምጃ ምክንያት፣

ሀ/ ዘሩን፣ ሃይማኖቱን፣ ዜግነቱን፣ የአንድ ማህበራዊ ቡድን አባልነቱን ወይም የፖለቲካ እምነቱን ምክንያት በማድረግ ማሳደድ፣ መሰቃየት ወይም መንገላታት ወደሚደርስበት አገር ወይም፣

## 8. Fundamental Change of Circumstances

1) Where the fundamental changes referred to in Article 7 (4) of this article are considered to have taken place in a country of nationality or of former place of habitual residence of a person or persons recognized as refugees under this Proclamation, the Head of the Authority, working in collaboration and co-ordination with the United Nations High Commissioner for Refugees, or its substitute and subject to such other special procedures as may be established for this purpose, initiate an assessment and verification of the nature and durability of the changes having regard to the circumstances which justified the grant of refugee status in the first place.

2) Following such assessment and verification, the Authority shall, in collaboration with the United Nations High Commissioner for Refugees, make a decision as to whether the refugee status of the person or group of persons concerned shall be declared to have cased.

3) The decision made pursuant to Sub-Article (2) of this Article shall also set out the consequences and implications for the refugee or refugees affected by the cessation of refugee status, including the right of individual refugees to have their individual claim for continuing refugee status examined.

## 9. Non - refoulement

1) No person shall be refused entry in to Ethiopia or expelled or returned from Ethiopia to any other country or be subject to any similar measure if as a result of such refusal, expulsion or turn or any other measure, such person is compelled to return to or remain in a country where:-

   a) he may be subject to persecution or torture on account of his race, religion, nationality, membership of a particular social group or political opinion: or

ለ/ በውጭ ወረራ ወይም የግዛት መያዝ በውጭ የአገዛዝ ሥልጣን ወይም የአገሪቱን ሕዝባዊ ሥርዓት ወይም ፀጥታ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በከባድ ሁኔታ በሚያናጋ ሁኔታ ህይወቱ፣ አካሉ፣ ሰብአዊነቱ ወይም ነፃነቱ አደጋ ላይ ወደሚወድቅበት አገር፣

እንዲመለስ ወይም በዚያው እንዲቆይ የሚያስገድደው ከሆነ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ አይከለከልም ወይም ከኢትዮጵያ እንዲባረር ወይም እንዲመለስ አይደረግም፣

፪/ ለአገር ደህንነት አስጊ ወይም ለሕብረተሰቡ አደገኛ ሆኖ ለተገኘ ወይም ከባድ ወንጀል ፈጽሞ በፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ጥፋተኛ የተሰኘ ማንኛውም ስደተኛ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ድንጋጌ ተጠቃሚ አይሆንም።

፫/ የዚህ አዋጅና የሌሎች ሕጎችን መንፈስ መሠረት በማድረግ የባለሥልጣኑ ኃላፊ አንድ ስደተኛ ለአገር ደህንነት አስጊ መሆኑን ይወስናል።

፲. ከአገር ስለማስወጣት

፩/ በሕጋዊ መንገድ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆነ ስደተኛ በብሔራዊ ፀጥታና በሕዝብ ሠላም ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ከአገር እንዲወጣ አይደረግም።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የማስወጣቱ ትዕዛዝ የሚሰጠው በባለሥልጣኑ ኃላፊ ነው። ይሁን እንጂ ኃላፊው ይህንን ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት ስደተኛው ጉዳዩን አቅርቦ እንዲያስረዳ ይፈቅድለታል።

፫/ ማንኛውም የማስወጣት ትዕዛዝ ከነምክንያቱ ለስደተኛው በጽሁፍ እንዲደርሰው ይደረጋል።

፬/ ከአገር እንዲወጣ በታዘዘ ስደተኛ ጥያቄ ሲቀርብ የማስወጣቱ ትዕዛዝ ስደተኛው በሌላ አገር ለመኖር እንዲፈቀድለት ለማመልከት እንዲያስችለው በቂ ለሆነ ጊዜ ሊዘገይ ይችላል።

b) his life, physical integrity or liberty would be threatened on account of external aggression, occupation, foreign domination of events seriously disturbing public order in part or whole of the country.

2) The benefit of this provision may not, however, be claimed by a refugee whom there are serious reasons for regarding as a danger to the national security, or who having been convicted by a final judgment of a particularly serious crime, constitute a danger to the community.

3) The Head of the Authority shall in line with the sprite of this Proclamation and existing Law determine whether serious grounds exist for regarding a refugee as a danger to national security.

**10. Expulsion**

1) A refugee who is lawfully resident in Ethiopia shall not be expelled except on the ground of national security and public order.

2) An order to expel, pursuant to Sub Article /1/ of this Article shall be made by the Head of the Authority. However, before making such an order, the Head shall allow the concerned refugee to present his case.

3) Any expulsion order shall be communicated in writing to the refugee together with the reasons for the order.

4) The execution of any expulsion order may, if the concerned refugee requests, be delayed for a reasonable period to enable such refugee, to seek admission to a country other than the country to which he is to be expelled.

**፲፩. ለጊዜው በእስር ስለማቆየት**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ መሠረት ከአገር እንዲወጣ የታዘዘው ሰው ትዕዛዙ እስኪፈጸም ወይም ከአገር እስኪወጣ ድረስ የኢትዮጵያን ደህንነት ወይም የሕዝቡን ሠላም እንዳያውክ ወይም ትዕዛዝን ለመፈፀም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በባለሥልጣኑ ኃላፊ ትዕዛዝ ሊያዝና ለጊዜው ሊታሰር ይችላል።

**፲፪. የቤተሰብ አንድነት**

፩/ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የጥገኝነት ጠያቂው ቤተሰቦች ወይም የቤተሰብ አባል የጥገኝነት ጥያቄው ጉዳይ ውሣኔ እስኪያገኝ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመግባትና ለመቆየት ይፈቀድላቸዋል።

፪/ የጥገኝነት ጠያቂው ቤተሰቦች ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉበት ጊዜ ጥገኝነት ጠያቂው ያለው መብት ተጠቃሚ እና ለግዴታ ዎቹም ተገዥ ነው።

፫/ እውቅና ያገኘ የስደተኛ ቤተሰብ አባል የሆነ ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ወደ ኢትዮጵያ መግባትና መቆየት ይፈቀድለታል።

፬/ እውቅና ያገኘው ስደተኛ ቤተሰብ አባል ኢትዮጵያ ውስጥ ባለበት ጊዜ ሁሉ ስደተኛው ያለው መብት ተጠቃሚና ለግዴታዎቹም ተገዥ ነው።

፭/ ይህ አንቀጽ የጥገኝነት ጠያቂና እውቅና ያገኘ ስደተኛ ቤተሰብ አባል ኢትዮጵያ ውስጥ ባለ ጊዜ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ መሠረት የስደተኝነት ማመልከቻ ከማቅረብ አይከለክለውም።

## ክፍል ሦስት
## የስደተኛነት እውቅና እንዲሰጥ ስለሚቀርብ አቤቱታና የስደተኛነት ሁኔታ አወሳሰን ሥነሥርዓት

**፲፫. የስደተኛነት እውቅና እንዲሰጥ ስለሚቀርብ አቤቱታ**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በድንበር ላይ ሆኖ ወይም በማንኛውም መግቢያ በር በሕጋዊም ሆነ ሕጋዊ ባልሆነ ሁኔታ ወደ ኢትዮጵያ የገባ እና ኢትዮጵያ ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት በስደተኝነት ለመቆየት የፈለገ ማንኛውም ሰው በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ባቅርብ ለሚገኝ፣

**11. Temporary Detention**

A person whose expulsion has been ordered under Article 10 of this proclamation may be arrested or detained upon the order of the Head of the Authority pending his expulsion if such detention is necessary for purposes of effecting the expulsion order or to ensure that he does not endanger the security or public order of Ethiopia pending the expulsion.

**12. Unity of the Family**

1/ A member of the family of an asylum-seeker as provided for in this Proclamation shall be permitted to enter and remain in Ethiopia until his case is finally decided.

2/ Once the family of an asylum-seeker are in Ethiopia, they shall be entitled to all the rights and be subject to all the duties of an asylum-seeker.

3/ A member of the family of a recognized refugee, as provided for in this Proclamation, shall be permitted to enter and remain in Ethiopia.

4/ Once the family of a recognized refugee is in Ethiopia, they shall be entitled to all the rights and be subject to all the duties of a recognized refugee.

5/ Nothing in this Article shall prevent a member of the family of an asylum-seeker or recognized refugee from himself applying for recognition and being recognized as a refugee in terms of Article 4 of this Proclamation.

## Part Three
## Application for Recognition of Refugee Status and Procedures for Determination of Refugee Status

**13. Application for recognition of Refugee Status**

1/ Without prejudices to Article 19 of this Proclamation, any person who is at the frontier or any other entry point or within Ethiopia, whether he has entered the country lawfully or otherwise, and who wish to remain within the country as a refugee in terms of this Proclamation, shall, within fifteen days apply to the nearest:-

/ሀ/ የባለሥልጣኑ ጽ/ቤት፣ ወይም
/ለ/ ፖሊስ ጣቢያ ማመልከቻውን

ማቅረብ አለበት።

፪/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ማመልከቻ የተቀበለ ፖሊስ ጣቢያ ማመልከቻውን ወዲያውኑ ለባለስልጣኑ ማስተላለፍ አለበት።

፫/ አመልካቹ በባለሥልጣኑ የሚዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት የሰጠው መግለጫ እውነት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

፬/ ባለሥልጣኑ ለአመልካቹ ጥገኝነት ጠያቂ መሆኑን የሚገልጽ የመታወቂያ ወረቀት መስጠት አለበት።

፭/ በሌላ ሕግ ተቃራኒ ድንጋጌ ቢኖርም ለስደተኝነት ባመለከተ ወይም በማመልከት ላይ በሚገኝ ሰው ላይ ሀገር ውስጥ በመግባት ወይም በሀገር ውስጥ በመገኘቱ ምክንያት የወንጀል ክስ አይቀርብም ወይም ክስ አይቀጥልም።

## ፲፬. በባለሥልጣኑ ስለሚሰጥ ውሳኔ

፩/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ መሠረት የሚቀርብ አቤቱታን መርምሮ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ የተደነገገው መስፈርት መሟላቱን ሲያረጋግጥ ለአመልካቹ የስደተኝነት እውቅና ይሰጣል።

፪/ ባለሥልጣኑ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት፣

/ሀ/ አመልካቹ ጉዳዩን አቅርቦ ለማስረዳት በቂ ጊዜ የተሰጠው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

/ለ/ ጉዳዩ በሚሰማበት ጊዜ ለአቤቱታ አቅራቢው ብቁ አስተርጓሚ መመደብ አለበት።

/ሐ/ የሚሰጠውን ውሳኔ ከነምክንያቱ አቤቱታ አቅራቢው በጽሁፍ እንዲያውቅ ማድረግ አለበት።

/መ/ እያንዳንዱን የቀረበለትን ጉዳይ በተገቢው ጊዜ ውሳኔ እንዲያገኝ ማድረግ አለበት።

/ሠ/ በምርመራውና በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ኮሚሽነር በታዛቢነት እንዲገኝ መጋበዝ አለበት።

፫/ በባለሥልጣኑ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አቤቱታ አቅራቢ ውሳኔውን በሰማ በሠላሳ ቀናት ውስጥ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ መሠረት ለተቋቋመው የይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ይግባኙን በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል።

a) office of the Authority; or
b) police station.

2/ The police station receiving the application shall, as soon as possible forward the application to the Authority.

3/ The applicant shall fill relevant forms and vouch for the truth of the statement therein.

4/ The Authority shall provide the applicant with identity card attesting to his status as asylum-seeker.

5/ Notwithstanding the provisions of any other law to the contrary, no criminal proceedings shall be commenced or continued against a person who has applied or is about to apply pursuant to this Proclamation on the account of his illegal entry and presence in the country.

## 14. Decision by the Authority

1) The Authority shall decide on the application presented to it in accordance with Article 13 of this proclamation.

2) In deciding asylum application, the Authority shall:-
   a) ensure that every applicant is given reasonable time to present his case;
   b) ensure the presence of qualified interpreter during all the stages of the hearing;
   c) cause the person concerned to be notified of its decision and the reason thereof in writing;
   d) decide on every application or case referred to it within reasonable period of time; and
   e) invite the United Nations High Commissioner for Refugees to participate as an observer.

3/ Any asylum-seeker, who is aggrieved by the decision of the Authority, may within thirty days of being notified of such a decision, appeal in writing to the Appeal Hearing Council established under Article 15 of this Proclamation

**፲፭. የይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ስለመቋቋም**

በስደተኝነት ለመቆየት የሚቀርብን አቤቱታ በሚመለከት ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርብን ቅሬታ የሚመለከት ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል::

**፲፮. የይግባኝ ሰሚ ጉባዔ አባላት**

፩/ ይግባኝ ሰሚ ጉባዔው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል::
   ሀ/ የባለሥልጣኑ ተወካይ. . . ...... ሰብሳቢ
   ለ/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተወካይ.... አባል
   ሐ/ የፍትሕ ሚኒስቴር ተወካይ . ....... "
   መ/ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ተወካይ ሁለት ተወካዮች..... . . . አባል

፪/ የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ኮሚሽነር በታዛቢነት እንዲሳተፍ በጉባዔው ይጋበዛል::

፫/ ባለሥልጣኑ ለጉባዔው ፀሐፊ ይመድባል::

**፲፯. የይግባኝ ሰሚ ጉባዔው ተግባር**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ወይም አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ /፫/ መሠረት የሚቀርቡለትን ይግባኝ መርምሮ ይወስናል፣

፪/ ጉባዔው የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት፣
   /ሀ/ አመልካቹ ጉዳዩን አቅርቦ ለማስረዳት በቂ ጊዜ የተሰጠው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት::
   /ለ/ ጉዳዩ በሚሰማበት ጊዜ ለአቤቱታ አቅራቢው ብቁ አስተርጓሚ መመደብ አለበት::
   /ሐ/ የሚሰጠውን ውሳኔ ከነምክንያቱ ለአቤቱታ አቅራቢው በጽሁፍ እንዲያውቅ ማድረግ አለበት::
   /መ/ እያንዳንዱን የቀረበለትን ጉዳይ በተገቢው ጊዜ ውሳኔ እንዲያገኝ ማድረግ አለበት::

፫/ ጉባዔው የራሱን ስብሰባ ሥነሥርዓት የሚወስን ውስጠ ደንብ ያወጣል::

**፲፰. ስለመዛግብትና ቃለጉባዔዎች አያያዝ**

በስደተኝነት ለመቆየት የቀረበ አቤቱታን የሚመለከቱ መዛግብት እና ቃለ ጉባዔዎች የስደተኛውን ጥበቃና ደህንነት ለአደጋ እንዳያጋልጡ ሆነው በምስጢር መጠበቅ አለባቸው::

**15. Establishment of an Appeal Hearing Council**

The Appeal Hearing Council that review the decision of the Authority in relation to asylum is here by established under this Proclamation.

**16. Member of the Appeal Hearing Council**

1) The appeal haring Council shall have the following members:
   a) The representative of the Authority ............................ Chairman
   b) The representative of the Ministry of Foreign Affairs....... Member
   c) The representative of the Ministry of Justice ........... "
   d) Two representatives of the Federal Affairs.
2) The United Nations High Commissioner for Refuges shall be invited to participate as an observer.
3) The Authority shall appoint asecratery for the Council....

**17. Functions of the Appeal Hearing Council**

1/ The Council shall decide on appeals submitted to it in accordance with Sub-Article (2) of Article 6 or Sub-Article (3) of Article 14 of this Proclamation.

2/ In the exercise of its function, the Council shall:-
   a) ensure that every applicant is given reasonable time to present his case;
   b) ensure the presence of qualified interpreter during all the stages of the hearing;
   c) decide on every application or case referred to it within reasonable period of time;
   d) cause the person concerned to be notified of its decision and the reasons thereof in writing; and

3/ The Council shall issue its own rules of procedure.

**18. Records and Minutes**

The records and minutes of meetings in relation to application for refugee status shall be kept in a confidential and secure manner so that the safety and security of an asylum-seeker may not be in danger.

**፲፱. ለተወሰኑ የሰዎች ቡድን የስደተኛነት እውቅና ስለመስጠት**

የባለሥልጣኑ ኃላፊ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬/፫/ የተደነገገውን መስፈርት የሚያሟሉ የአንድ የሰዎች ቡድን ስደተኞች ናቸው ሊል ይችላል።

## ክፍል አራት

## የስደተኛነት እውቅና ጠያቂዎች እና እውቅና ያገኙ ስደተኞች መብቶችና ግዴታዎች

**፳/ የጥገኝነት ጠያቂዎች መብቶችና ግዴታዎች**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ እና አንቀጽ ፲፱ መሠረት የስደተኛነት እውቅና እንዲሰጠው የመለከተ ማንኛውም ሰው፣

ሀ/ ባለሥልጣኑ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስ ኪሰጥ ድረስ፣ ወይም

ለ/ ማመልከቻው ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረ እንደሆነ የይግባኝ መብቱ እስኪያበቃ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲቆይ ይፈቀድለታል።

፪/ የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች ከዚህ አዋጅ ዓላማ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ላይ ያሉ ሕጎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ስር በተገለፀ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

**፳፩/ እውቅና ያገኙ ስደተኞች መብቶችና ግዴታዎች**

፩/ ማንኛውም እውቅና ያገኘ ስደተኛ፣

ሀ/ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር ይፈቀድለታል፣

ለ/ ስደተኝነቱን የሚገልጽ የመታወቂያ ወረቀት ይሰጠዋል፣

ሐ/ የስደተኞች የጉዞ ሠነድን በሚመለከት በተደረገ አለምአቀፍ ስምምነት መሠረት ወደውጭ አገር ለመጓዝ የሚያስችል የጉዞ ሰነድ ይሰጠዋል፣

**19. Declaration of class of Persons as Refugees**

If the Head of the Authority considers that any class of persons met the criteria under Article 4(3) of this Proclamation, he may declare such class of persons to be refugees.

## Part Four

## Rights and Obligations of Asylum-seekers and Recognized Refugees

**20. Rights and Obligations of an Asylum-seeker**

1) Any person who has applied pursuant to Article 13 and Article 19 of this Proclamation for recognition of his status as a refugee shall be allowed to remain in Ethiopia:-
   a) until the Authority decides on his application; or
   b) if his application is unsuccessful, until he exhausts his right of appeal.

2) Any person stated under Sub-Article (1) of this Article shall, except to the extent that the provisions of any other law may be inconsistent with the purposes of this Proclamation, be subject to laws in force within Ethiopia.

**21. Rights and Obligations of Recognized Refugees**

1) Every recognized refugee shall:-
   a) be permitted to remain within Ethiopia in accordance with the provision of this Proclamation;
   b) be issued with identity card attesting to his refugee status;
   c) be issued with a travel document for the purpose of traveling outside Ethiopia in accordance with international agreement;

መ/ በስደተኛ ኮንቬንሽንና በአፍሪካ አንድነት ድርጅት የስደተኞች ኮንቬንሽን በተደነገጉ ሌሎች መብቶች ሁሉ ይጠቀማል፣ ግዴታዎችንም ያከብራል፣

ሠ/ ከዚህ አዋጅ ዓላማዎች የሚቃረን ካልሆነ በስተቀር በኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ላይ ባሉ በማናቸውም ሕጎችና ድንጋጌዎች ይገዛል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ /መ/ የተደነገገው ቢኖርም የባለሥልጣኑ ኃላፊ በኢትዮጵያ ውስጥ እውቅና ያገኙ ስደተኞችና ቤተሰቦች፣ በስደተኛነት እውቅና ለማግኘት ያመለከቱ ሰዎችና ቤተሰቦች የሚኖሩባቸውን ቦታዎችና አካባቢዎች ሊወስን ይችላል፡፡ ሆኖም የሚወሰነው የመኖሪያ ቦታ ጥገኝነት ጠያቂዎች ከመጡበት ሥፍራ ወይም ከቀድሞው መደበኛ መኖሪያ አገራቸው ተገቢው ርቀት እንዲኖረው በማድረግ መወሰን አለበት፣

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ /መ/ የተደነገገው ቢኖርም እያንዳንዱ እውቅና ያገኘ ስደተኛ፣ በስደተኛነት እውቅና ለማግኘት ያመለከቱ ሰዎች እና ቤተሰቦቻቸው በምንዳ መቀጠርንና ትምህርትን በተመለከተ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት የኢትዮጵያ ዜጎች ያልሆኑ ሰዎች በተሰጡ ተመሳሳይ መብቶች ይጠቀማሉ፡፡ በተጣሉባቸው ግዴታዎችም ይገዛሉ፡፡

## ፳፪/ ለጥቃት ለሚጋለጡ ልዩ ጥበቃ ስለመደረጉ

ባለሥልጣኑ ለጥቃት ለሚጋለጡ ስደተኛ ሴቶች፣ ስደተኛ ህፃናት፣ ስደተኛ አረጋውያንና የአካል ጉዳተኞች ልዩ ጥበቃ ማድረግ አለበት፡፡

## ፳፫/ በፈቃደኝነት ወደ አገር ስለመመለስ

፩/ እያንዳንዱ እውቅና ያገኘ ስደተኛ በራሱ ምርጫ ከኢትዮጵያ ወደዜግነት አገሩ ወይም ወደ ቀድሞ መደበኛ መኖሪያ ቦታው ደህንነቱና ክብሩ ተጠብቆለት ለመመለስ የመጠየቅ መብት አለው፣

d) be entitled to other rights and be subject to the duties contained in the Refugee Convention and the OAU Refugee Convention;

e) except to the extent that the provisions of any other law may be inconsistent with the purposes of this Proclamation, be subject to the laws in force within Ethiopia; and

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) (d) of this Article, the Head of the Authority may designate places and areas in Ethiopia within which recognized refugees, persons who have applied for recognition as refugees, and family members thereof shall live, provided that the areas designated shall be located at a reasonable distance from the border of their country of origin or of former habitual residence.

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) (d) of this Article, Every recognized, refugee, and family members thereof shall, in respect to wage earning employment and education, be entitled to the same rights and be subjected to the same restrictions as are conferred or imposed generally by the relevant laws on persons who are not citizens of Ethiopia.

## 22. Special Protection to Vulnerable Groups

The Authority shall take measures to ensure the protection of women refugees, refugee children elderly refugees and handicap who needs special protection.

## 23. Voluntary repatriation

1) Every recognized refugee has the right, of his own volition, to seek to repatriate from Ethiopia to his country of nationality or former habitual residence in safety and dignity.

፪/ እውቅና ያገኘ ስደተኛ ቤተሰብ አባል ወደዜግነት አገሩ ወይም ወደቀድሞ መደበኛ መኖሪያው ቢመለስ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ በተመለከቱት ምክን ያቶች መሰደድ ይደርስበታል ወይም አደጋ ያጋጥመዋል የሚያስብል በቂ ምክንያት ከሌለ በስተቀር እውቅና ያገኘው ስደተኛ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት በራሱ ፈቃድ ወደ አገሩ ለመመለስ ከወሰነ ይኸው ውሳኔ ከሱ ጋር ያሉ ሁሉም የቤተሰብ አባላት ውሳኔ እንደሆነ ይቆጠራል።

2) A voluntary decision by a refugee to repatriate in terms of Sub-Article (1) of this Article shall be deemed to be a decision of all members of his family accompanying him, save where it appears that such family member of family members is or are likely, upon return to the country of nationality or former habitual residence, to be persecuted or be placed in danger for the reasons set out in Article 4.

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## Part Five
## Miscellaneous Provisions

### ፳፬/ ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ማንኛውም ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን አዋጅ፣ ደንብ፣ ትዕዛዝ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

### 24. Inapplicable Laws

Any Proclamation, regulation, order or directive which is inconsistent with this Proclamation shall not apply to matters provided for in this Proclamation.

### ፳፭/ ስለቅጣት

የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የጣሰ ማንኛውም ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል።

### 25. Penalty

Whosoever violates or obstructs the implementation of this Proclamation shall be punishable in accordance with the Penal Code of Ethiopia.

### ፳፮/ ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ በሚገባ ሥራ ላይ ለማዋል ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

### 26. Power to issue regulations

The Council of Ministers may issue regulations for the proper implementation of this Proclamation.

### ፳፯/ አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

### 27. Effective date

This Proclamation shall come into force on the date of its Publication in the Federal Negarit Gazette.

አዲስ አበባ ሰኔ ፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**Done at Addis Ababa, 15th day of June, 2004.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OFETHIOPIA**